
# በ‹‹ታሪክን በቅኔ›› መጽሐፍ ላይ የቀረበ አጭር ዳሰሳ

**ሰሎሞን ተሾመ**[1]




## መግቢያ

በተለያዩ ማህበራዊ ሁነቶች ላይ ያላቸውን የሀገረሰባዊ ሙዚቃና የቃል ግጥም ክህሎት የሚያቀርቡ ግለሰቦች ከዋኞች (performers) ይባላሉ፡፡ ከዋኞች ባላቸው የዕውቀትና የክህሎት ደረጃ የተለያዩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ከዋኞች መካከል ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው፣ ጥበባቸውን ከንጉስ ሸንጎ ፊት የሚያቀርቡ፣ ታሪክ ዘጋቢና የመገናኛ ብዙሃንን ሚና የሚጫወቱ ባለሙያ ከዋኞች (specialists) በሚል ይጠራሉ፡፡ የሀገረሰባዊ ሙዚቃ ምሁራን ከባለሙያ ከዋኞች መካከል እጅግ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን ‹‹ባርድ›› (bard) በሚል ማዕረግ ይጠሯቸዋል፡፡

በሀገራችን ከፍተኛ ችሎታ ካላቸውና ‹‹ባርድ›› በሚል ስያሜ ሊጠሩ የሚችሉ የሙዚቃና የቃል ግጥም ባለሙያዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ጥቂት የሀገራችን አዝማሪዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ለምሳሌ፡- በንጉሥ ሣህለሥላሴ ዘመን አዝማሪ የነበረችው ጦጢት፣ በንጉሥ ምኒልክ ዘመን አዝማሪ የነበሩት ፊት አውራሪ ውቤ ጎሹ እና ሐሰን አማኑ፣ የደጅ አዝማች ጎሹ አዝማሪ ጣፋጭ፣ የልጅ እያሱ አዝማሪ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ እንዲሁም የራስ ጉግሳ አዝማሪ ቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ ባለሙያዎች የዘመን ታሪክ ዘጋቢ ናቸው፡፡ በሕይወት ገጠመኛቸው፣ በግጥሞቻቸው ታሪክ ይነግራሉ፣ ታሪክ ይመዘግባሉ፣ ለመጪው ትውልድም ታሪክ ያስተላልፋሉ፡፡ በመሆኑም የእነሱን ሕይወትና በወቅቱ የገጠሟቸውን ቃል ግጥሞች ማጥናት በዘመኑ የነበረውን ሁነት ለማወቅ ይረዳል፡፡ ይህን መሰል የግለታሪክና የቃል ግጥም ጥናት የአንድ ማህበረሰብን የትናንት

[1] የፎክሎር ጥናት ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር፤ የፎክሎር ጥናት ትምህርት ክፍል ፤ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ ባህር ዳር ፤ኢትዮጵያ፡፡
*Corresponding author: solomontesh12@gmail.com*

ሕይወቱን፣ ታሪኩንና ባህሉን በትውስታዊ ምልሰት የሚያሳየን ነው፡፡ ይህም የወቅቱን የዘመን መንፈስ በግልጽ እንድንረዳ ያደርገናል፡፡

*ታሪክን በቅኔ* (2008 ዓ.ም) የተሰኘው መጽሐፍ በደራሲ በሁሉም አለበል የተዘጋጀ ነው፡፡ይህ መጽሐፍ የቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ ሕይወትና ስራዎቻቸው ላይ የቀረበ ነው፡፡ ደራሲ በሁሉም አለበል፤ ከዚህ መጽሐፍ በተጨማሪ በራስ ጉግሳ ወሌ የሕይወት ታሪክ ላይ የሚያተኩር *የተዳፈነው ታሪክ* የተሰኘ መጽሐፍ *የተዋጡ ድምጾች እና ውስብስብ ውሎዎች የተሰኙ ሁለት የአጫጭር ልብ ወለዶች ስብስብ እንዲሁም የሸምበቆ ባህር* እና *ሳምራዊት* የተሰኙ ሁለት የግጥም ስብስቦች መጻሕፍት ደራሲ ስትሆን ከእነዚህ በተጨማሪ ከሌሎች ደራሲዎች ጋር በጋራ ስድስት መጻሕፍትን አሳትማለች፡፡

በሁሉም አለበል *ታሪክን በቅኔ* በሚል ርዕስ ያዘጋጀችውና ከላይ በፎቶ ግራፍ የቀረበው መጽሐፍ የአያቷ የህይወት ታሪክ ነው፡፡ ደራሲዋ ከልጅነቷ ጀምሮ ቀኝ አዝማች ምስጋናው ስለነበራቸው ሕይወትና ስራዎች አባቷ የሚነግሯትን ስትሰማ አድጋለች፡፡ በሁሉም አለበል ከአባቷ አስደማሚና አስደናቂ ትረካዎች አልፋ የአያቷን ጉዳይ በጥናትና ምርምር አስደግፋ በመጽሐፍ መልክ ለአንባቢ አቅርባለች፡፡

**የመጽሐፉ ይዘት አጭር ዳሰሳ**

*ታሪክን በቅኔ* መጽሐፍ 164 ገጾች ያሉት ሲሆን በ2008 ዓ.ም ለህትመት የበቃ ነው፡፡ መጽሐፉ ሦስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ የመጀመሪያው ክፍል ‶መግቢያ‶፣ ‶መሰናዘሪያ‶ እና ‶ብዕር ማንሻ‶ የሚሉ ንዑስ ርዕሶችን ይዟል፡፡ሁለተኛው ክፍል አስር ንዑስ ርዕሶችን ይዟል፡፡ በሦስተኛው ክፍል አባሪዎች፣ የመረጃ ሰጪዎች ስም ዝርዝር እና ዋቢዎች ተካተዋል፡፡

ይህ መጽሐፍ የቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ ሕይወትና ስራዎቻቸው ላይ የቀረበ ነው፡፡ ቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ የራስ ጉግሳ ወሌ አዝማሪ የነበሩ ሲሆን ከ1883 ዓ.ም እስከ 1964 ዓ.ም የኖሩ ናቸው፡፡ ቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ ከአባታቸው ከአቶ አዱኛ ኃይሉ እና ከእናታቸው ወ/ሮ አሳይታ ወልዱ በ1883 ዓ.ም በደቡብ ጎንደር ዞን፤ ከምከም ቃሮዳ ወረዳ ተወለዱ፡፡ እድገታቸውም በተወለዱበት ከምከም ቃሩዳ ነው፡፡

ቀኝ አዝማች ምስጋናው እድገታቸው በቤተክርስቲያን ትምህርት የታነጸ ሲሆን በወቅቱም ከፊደል ቤት እስከ መጽሐፍ ቤት ተምረዋል፡፡ ቅኔም ተቀኝተዋል፡፡ ገና በለጋ እድሜያቸው ባላቸው የግጥምና የቅኔ ችሎታ ከፍተኛ አድናቆት ማግኘት ቻሉ፡፡ እድሜያቸው ከፍ ሲልም በቤተመንግስት በመገኘት ግጥሞቻቸውንና ቅኔዎቻቸውን በዜማ ማቅረብ ጀመሩ፡፡ ይህን ችሎታቸውን ያዩት በወቅቱ የበጌምድር ገዢ የነበሩት ራስ ጉግሳ ወሌ ከእሳቸው ዘንድ እንዲኖሩ በማድረጋቸው ኑሯቸውን ደብረ ታቦር ከተማ አደረጉ፡፡ ራስ ጉግሳ ወሌ የእቴጌ ጣይቱ ብጡል ወንድም የራስ ወሌ ብጡል ልጅ ናቸው፡፡ የንግስት ዘውዲቱ ምኒልክ ባለቤት ነበሩ፡፡ ቀኝ አዝማች ምስጋናው ከወጣትነት ጀምሮ እስከ ራስ ጉግሳ ወሌ ሕልፈተ ሕይወት ድረስ የራስ ጉግሳ ወሌና የባለቤታቸው ንግስት ዘውዲቱ ምኒልክ አዝማሪ በመሆን አገልግለዋል፡፡

ቀኝ አዝማች ምስጋናው የተለያዩ ግጥሞችና ቅኔዎች በማቅረብ በወቅቱ እጅግ በጣም ታዋቂና ተወዳጅ ባለሙያ ነበሩ፡፡ ግጥሞቻቸውና ቅኔዎቻቸውም የግል የሕይወት ገጠመኝን፣ በወቅቱ ያጋጠሙ ማህበራዊ ጉዳዮችን፣ በራስ ጉግሳ ወሌ ላይ ያጋጠሙ ሁነቶችን፣ በወቅቱ ያጋጠሙ ታሪካዊ ገጠመኞችን ወዘተ. መሰረት በማድረግ የተቀኟቸው እንደሆኑ ታሪክን በቅኔ በተሰኘው በዚህ መጽሐፍ ተብራርቷል፡፡

ቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ ለበርካታ አመታት የራስ ጉግሳ ወሌ የቅርብ ሰውና ባለሟል በመሆን አብረዋቸው አሳልፈዋል፡፡ ከዚህም ባለፈ ለራስ ጉግሳ ወሌ ከፍተኛ ፍቅር ነበራቸው፡፡

ይህን ፍቅራቸውንም ከገለጹባቸው ግጥሞች መካከል የሚከተለው መንቶ በመጽሐፉ ውስጥ ይገኛል፤

አምላክ ሲፈጥርህ እኔ ካንተ አድሬ

በሞት የማይሻር ከአንተ ኖረ ፍቅሬ፡፡

በማለት ቀኝ አዝማች ምስጋው ለራስ ጉግሳ የነበራቸውን ልባዊና ሞት እንኳን የማይሽረው ፍቅር እንደነበራቸው በግጥም ገልጸዋል፡፡ ራስ ጉግሳ ወሌም በተመሳሳይ ለቀኝ አዝማች ምስጋናው ልባዊ አክብሮት ነበራቸው፡፡ ለእሳቸውም፤ የሊቀ መኳስነት እና የቀኝ አዝማችነት ማዕረግ የሰጧዋቸው ራስ ጉግሳ ወሌ ናቸው፡፡ ይህን ማዕረግም በ1939 ዓ.ም ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ አጽድቀውላቸዋል፡፡

በአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን እና በንጉስ ሚካዔል መካከል ሰገሌ ላይ በተደረገው ጦርነት፤ ራስ ጉግሳ ወሌ በተፈሪ መኮንን ወገን በግራ ግምባር ከእነ ራስ ናደው አባወሎ፣ ከእነ ራስ ደምሰው ነሲቡ እና ከሌሎች አበጋዞች ጋር ተሰልፈዋል፡፡ ከድሉ በኋላ የራስ ጉግሳ ጦር ሸዋ በመከረሙ ምክንያት፣ በቤተሰብ ናፍቆት መቸገሩን ጦሩ ለቀኝ አዝማች ምስጋናው በነገራቸው ጊዜ፡-

አጥብቆ ጨነቀኝ ልቤ ተበትኖ

እንጀራዬ ሸዋ ቤቴ ጎንደር ሆኖ፡፡

በማለት ገጥመዋል፡፡ ይህንንም አልጋ ወራሽ ተፈሪ ሰምተው የራስ ጉግሳ ጦር ወደ ጎንደር እንዲሄድ ማድረጋቸው በመጽሐፉ ተዘግቧል፡፡

ራስ ጉግሳ ወሌ ከባለቤታቸው ከንግስት ዘውዲቱ ጋር የነበራቸው ትዳር እንዲቋረጥ ተደርጎ ወደ ተሰጣቸው አማራ ሳይንት ግዛት ሄዱ፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ስልጣን ከሸዋ ወደ ጎንደር እንዳይዛወር ከሚል እንደሆነ ይነገራል፡፡ መስከረም 1921 ዓ.ም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን የንግስና ሥርዓት ፈጸሙ፡፡ በዚህ ወቅት "ስልጣኑን ንጉሡ ሊጠቀልል ነው፤ በንግስት ዘውዲቱ ላይ የተካሄደ ሴራ ነው" የሚል ሀሳብ በመዛመቱና ራስ ጉግሳ በንጉሱ ላይ ቂም በመያዛቸው ለጦርነት ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ፡፡ በዚህ ወቅት ሕዝቡ ለሁለት ወገን ተከፍሎ ነበር፡፡ ይህንንም ቀኝ አዝማች ምስጋናው፡-

አባ ደልድል ጉግሳ አትመን ሰው

በልጅግህን አጉርሰህ ተንተራሰው

ጥይትህን አጉርሰህ ተንተራሰው

መሃላ ደፋር ነው የዛሬ ዘመን ሰው፡፡

በማለት ስጋታቸውን በግጥም መግለጻቸው በመጽሐፉ ተመላክቷል፡፡ በንጉስ በኩል የራስ ጉግሳ ወሌ የወንድም ልጅ የሆኑት ደጃዝማች አያሌው ብሩ ወደ ጦር ሜዳ ዘምተው ነበር፡፡ በግርማዊ ንጉስ ነገስት አጼ ኃይለሥላሴ እና በራስ ጉግሳ ወሌ መካከል መጋቢት 22 ቀን 1922 ዓ.ም ልዩ ስሙ አንቺም በተባለ ሜዳ ጦርነት ተካሄደ፡፡ በጦርነቱ ላይ ሁለት ‹‹ፓቴዝ›› የጦር

አውሮፕላኖች ቦምብ በመጣልና መትረስ በመተኮስ ከመንግስት ጦር ጎን ተሰልፈዋል፡፡[2] በዚህ ወቅት ቀኝ አዝማች ምስጋናው

ወይ የሼዎች ነገር ሁል ጊዜ በመላ

አመዴን በቅጠል ጉግሳን በአውሮብላ፡፡

*** *** ***

አውሮብላ እሚሏት ክፉ አውሬ መጥታ

ሸዋን አስታጠቀች የእኛን ሱሪ ፈታ፡፡

*** *** ***

ወገራ አሳላፊ ደምቢያ እንጀራ ጣይ

ተበላህ ጎንደሬ አትነሳም ወይ፡፡

በማለት ገጥመዋል፡፡ በአንቺም ጦርነት ላይ ራስ ጉግሳ ወሌ ተገደሉ፡፡ ቀኝ አዝማች ምስጋናው የራስ ጉግሳን ሞት ሲሰሙ፣ ሀዘናቸውን በሚከተለው መንቶ ገልጸዋል፤

እመቤቴ ማርያም እስከዛሬ ድረስ አማላጅ ነበርሽ

እንደሌላው ሁሉ አንቺም ሰው ገደልሽ፡፡

በዚህ ጦርነት ላይ ዘመዳቸው ደጃዝማች አያሌው ብሩ ከመንግስት ወገን ሆነው ራስ ጉግሳን ስለወጉ፤ ቅሬታቸውን በግጥም እንደሚከተለው ገልጸዋል፤

በሸዋ በትግሬ መሳበቡ ምነው

ጉግሳን የገደለው አያሌው ዘመድ ነው፡፡

ደጃዝማች አያሌው ብሩ ለመንግስት ጦር የወገኑት ከነበራቸው የስሜን ገዢነት ወደ በጌምድር ገዢነት እንደሚቀየሩ ቃል ስለተገባላቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡ ነገር ግን ከጦርነቱ በኋላ የተገባላቸው ቃል ተቀይሮ የየጁ ገዢ ሆነው በመሾማቸው ቀኝ አዝማች የሚከተለውን ገጥመዋል፤

የሸዋ መኳንንት አገር ሲካፈሉ

የትግሬ መኳንንት አገር ሲካፈሉ

የሐረር መኳንንት አገር ሲካፈሉ

አባ ይርጋ አያሌው የጁን አገኘ አሉ፡፡

ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ቀኝ አዝማች ምስጋናው በደጃዝማች አያሌው ብሩ ጦር ስር በመሆን በሽሬ ግንባር ተሰልፈዋል፡፡ ከአርበኞች ጋርም በሽሬ፣ በዳባት፣ በወገራና በጸለምት ግንባሮች ዘምተዋል፡፡ በስፍራው ለነበሩት ጀግናው አርበኛ ራስ ውብነህ ተሰማ ወይም በቅጽል ስማቸው *አሞራው ውብነህ* ስለነበራቸው ጀግንነት እንዲህ በማለት ገልጸዋል፤

---

[2] - ከዚህ መረጃ በተቃራኒ በጦርነቱ ላይ አውሮፕላኖቹ ሰማይ ላይ በረሩ እንጂ ቦንብ አልጣሉም የሚል መረጃም እንዳለ ልብ ይሏል፡፡

የሮማ ነጭ በሬ ተከቧል በበረት

ሊበላው ነው አሉ አሞራው ዞረበት፡፡

በተለያየ ግንባር ያለው የኢትዮጵያ ጦር በፋሽስት ጣሊያን ጦር ተሸነፈ፡፡ ንጉሡም ወደ እንግሊዝ ሄዱ፡፡ በዚህ ወቅት ቀኝ አዝማች፡-

ያልተገራ ፈረስ ጠቅል እያላችሁ

ከማይጨው ፈርጥጦ ሎንዶን ገባላችሁ፡፡

በማለት ንጉሱን በግጥም ተችተዋል፡፡ ከንጉሡ ጋር አብረው የተሰደዱትን ልዑል ራስ ካሳ ኃይሉንም፡-

ጥጥም ተወደደ ሆነ ሙሉ መሉ

ወይዘሮ ራስ ካሳ ፈትለው እንዳይበሉ፡፡

በማለት በግጥም ተናግረዋቸዋል፡፡ ጣሊያን አገሪቱን ከያዘ በኋላ ቀኝ አዝማች ምስጋናው ሁለት መልክ ያዙ፡፡ በአንደኛው መልክ፤-

በዚች አገራችን ነጭ ጤፍ አይብቀል
አረም አስመስሎ ከነስሩ መንቀል፡፡
*** *** ****
ከእንግዲህ ኢትዮጵያ ጥቁር ጤፍ ይብቃን
ነጩን እየገዛን ለመብላት ያብቃን፡፡

በማለት ጣሊያንን ማንቋሸሽ ጀመሩ፡፡ በሁለተኛው መልክ ደግሞ በተቃራኒው፡-

ማመስገን ነው እንጂ ለምንድን ነው ማማት

ሮማ ተጋግሮ ጎንደር ምሳ መብላት፡፡

*** *** ***

ዶቼ መሶሎኒን ቀጥቃጭ ያለው ማነው

የቀጥቃጮች ቀጥቃጭ ኃይለሥላሴ ነው፡፡

በማለት ለጣሊያን ድጋፍ ሰጡ፡፡ ጣሊያን ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ ስልጣናቸው ተመለሱ፡፡ በዚህ ወቅት ጃንሆይ ‹‹እንግሊዝ እያለን ምን ብለህ ትሰድበን እንደነበር ስምተናል፡፡ የሞት ፍርድ ተፈርዶብሃል›› አሏቸው፡፡ ቀኝ አዝማችም ‹‹በስጋዬ ይፍረዱብኝ በጌታዬ በራስ ጉግሳም ፈርደዋል፡፡ ለነፍሴ ግን ፈጣሪ አለኝ›› አሉ፡፡ በአርበኞች ልመናም ይቅርታ ተደረገላቸው፡፡ በዚህ ጊዜም፡-

ሐምሌ 16 ቀን የወጣው ፀሐይ

ብርሃኑ አበራ በኢትዮጵያ ላይ፡፡

በማለት ጃንሆይን ሲያወድሱ፤ ጃንሆይ በመደሰታቸው የወርቅ ቀለበትና የፋርስ ምንጣፍ እንደሸለሟቸው በመጽሐፉ ተዘግቧል፡፡

በራስ ጉግሳ ሞት ምክንያት ቀኝ አዝማች ምስጋናው ከንጉስ ኃይለሥላሴ ጋር የነበራቸው ቅሬታ እንዳለ ቢሆንም በጣሊያን ወረራ ወቅት ቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ በ1928 ዓ.ም አራት ልጆቻቸውን ይዘው ከአርበኞች ጋር መቀላቀላቸው በመጽሐፉ ተዘግቧል፡፡ ጣሊያን ሀገሪቷን

ሙሉ ለሙሉ ከተቆጣጠረ በኋላ እሳቸው ለጣሊያን የማደራቸው ምክንያት ምን እንደሆነ በመጽሐፉ በግልጽ የቀረበ ነገር የለም፡፡ ይህ የቀኝ አዝማች ምስጋናው የእምነትና የአቋም እጥፋት በጥልቀት ቢዳሰስ የመጽሐፉን ስራ ይበልጥ የተሟላ ያደርገው ነበር፡፡

ከነጋድራስ ተሰማ እሸቴ በመቀጠል ቀኝ አዝማች ምስጋናው የሙዚቃ ስራዎቻቸውን በሸክላ ያሳተሙ ሁለተኛው ሰው መሆናቸው በመጽሐፉ ተገልጿል፡፡[3] ቀኝ አዝማች ምስጋናው በርካታ የሙዚቃ ስራዎችን ሰርተዋል፡፡ የእሳቸውን የሙዚቃ ስራዎች የቀደምትና የአሁን ዘመን ታዋቂ ዘፋኞች ድጋሚ ተጫውተዋል፡፡ ከእነዚህ ዘፋኞች መካከል ደርባባው አቡኔ፣ የዝና ነጋሽ፣ ይርጋ ዱባለ፣ ሙሉቀን መለሰ፣ ይሁኔ በላይ እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

እቴ አውይኝ ልዋል ከሹሩባሽ መሀል
እቴ አውይኝ ልዋል ከከንፈርሽ መሀል፤
ተይኝ አላልኩሽም ተኳኩሎ ሜዳ
ዐይን ወረተኛ ነው ያመጣል እንግዳ

የሚለው ‟እቴ አውይኝ ልዋል” የተሰኘ የሙዚቃ ግጥም የቀኝ አዝማች ምስጋናው ሲሆን፣ በድምጻዊ ሙሉቀን መለሰ ድጋሚ የተዘፈነ ነው፡፡

ከጥቂት አመታት በፊት ድምጻዊ ይሁኔ በላይ ባሳተመውና ‟ጉዛራ” በተሰኘው የሙዚቃ አልበም ውስጥ፤-

ምስጋናው ደግ ነው ለዕልፍኝ የሚበጅ

እርጅና በፈረስ ደረሰበት እንጅ፡፡

*** *** ***

እኔማ ጠገብኩሽ በሕልሜ እየመጣሽ

ላንቺ ይብላኝ እንጂ ምስጋናውን ያጣሽ፡፡

የሚሉ ስንኞች የተካተቱበት ሙዚቃ የቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ ስራ ሲሆን፣ ቀደም ሲል በሸክላ ካሳተሙት የሙዚቃ ስራ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡

እነዚህን ግጥሞች የቀኝ አዝማች ምስጋናውን ልዩ የሕይወት ገጠመኝና የሽምግልና እድሜ የሚገልጹ ይመስላሉ፡፡ ነገር ግን ቀኝ አዝማች ምስጋናው እነዚህን ግጥሞች መቼ እንደገጠሟቸውና በየትኛው የታሪክ ሁነት በመመስረት እንደገጠሟቸው የሚጠቁም መረጃ በመጽሐፉ አልተገለጸም፡፡ ይህ መረጃ በመጽሐፉ ተገልጾ ቢሆን በተሻለ ደረጃ የእሳቸውን ሕይወትና የዘመኑን የታሪክ ሁነት መረዳት ያስችል ነበር፡፡

በቀኝ አዝማች ምስጋናው ግጥሞች ከተገለጹ ታሪኮች መካከል በወቅቱ ስለነበሩ ጠጅ ቤቶች ይገኙበታል፡፡ በወቅቱ በጎንደር ከተማ ስመጥር የነበረው የአበቅየለሽ ጠጅ ቤትና ደብረታቦር ከተማ የነበረው የየኔገላ ጠጅ ቤት ይጠቀሳሉ፡፡ በእነዚህ ጠጅ ቤቶች ከተራው ሕዝብ ሌላ የዘመኑ ባላባቶችና ሹማምንት ጎራ ይሉ ነበር፡፡ ቀኝ አዝማች ምስጋናውም በዘመኑ ስለእነዚህ ጠጅ ቤቶች፤-

አይቆረጠምም ደረቁ ባቄላ

ጎንደር አበቅየለሽ ፋርጣ የኔ ገላ፡፡

[3] - በስፋት የሚታወቀው የነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ቢሆንም፤ በ1904 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የሙዚቃ ስራዎቻቸውን በጋራ በሸክላ ያሳተሙት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴና አቶ አስታጥቄ ሀብተወልድ ናቸው፡፡

በማለት በግጥማቸው ሲያወድሱ፤ የወ/ሮ አበቅየለሽን ቁንጅና ለመግለጽ ደግሞ፤

ከጠጁ ከማሩ ሌላ ምን አለሽ
ከቶ እንዲህ አድርጎ ያማረው ፊትሽ፡፡

ሲሉ በግጥማቸው ስለውበታቸው መጠየቃቸው በመጽሐፉ ተዘግቧል፡፡

## ማጠቃለያ

በደራሲ በሁሉም አለበል የተዘጋጀው *ታሪክን በቅኔ* የተሰኘው ይህ መጽሐፍ የቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ የሕይወት ታሪክና የእሳቸው ግጥሞች፣ ቅኔዎችና የሙዚቃ ስራዎች የተገለጸበት ነው፡፡ በመጽሐፉ የእሳቸው ግጥሞች በወቅቱ የነበረውን ታሪካዊና ማህበራዊ አውድ መሰረት በማድረግ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

ታሪክን በቅኔ መጽሐፍ፤ በታሪክ፣ በሙዚቃ፣ በፎክሎር፣ በሥነጽሑፍና በሌሎች የትምህርት መስኮች የተለመደውን አይነት የምርምር ሥነዘዴ የተከተለ ነው፡፡ ደራሲዋ ቀኝ አዝማች በሕይወት ከነበሩበት የዘመን ርቀት ምክንያት የመረጃ እጥረት ሊኖር የሚችልን ተግዳሮት ለመቅረፍ ያደረገችው የረጅም አመት የመስክ ምርምር ስራ፣ የመረጃዎችን ተዓማኝነት ለማረጋገጥ የሄደችበት መንገድ እንዲሁም የምርምር ስራ ዘዴን ለመተግበር ጥረት ማድረጓ ከፍተኛ አክብሮት የሚያስቸራት ጠንካራ ጎን ነው፡፡

እነዚህ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉ ሆነው፤ በመጽሐፉ ውስጥ መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል በዋናነት የታሪክ መረጃዎችና የታሪክ ሁነቶች በዓመተምህረት ሲገለጹ መጣረስ፣ አንድ የመረጃ ምንጭን ብቻ ማመንና ከሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች ጋር አለማማሳከር፣ በእሳቸው ሕይወት ላይ የመረጃ ክፍተትና የመረጃ ስሑነት መኖር፣ በመጽሐፉ የቀረቡ ግጥሞችና ቅኔዎች በትክክል የእሳቸው የፈጠራ ስራዎች ስለመሆናቸው የቀረቡ መረጃዎች አሳማኝ አለመሆን፡ ደራሲ በሁሉም አለበል የቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ የልጅ ልጅ በመሆኗ ከቤተሰባዊ ውግንና ለመውጣት ያደረገችው ጥረት አናሳ መሆን እንዲሁም የመጽሐፉ አጠቃላይ ቅንብር/አደረጃጀት ላይ ክፍተት መኖር ናቸው፡፡ እነዚህ ድክመቶች በቀጣይ የሕትመት ጊዜ ቢስተካከሉ መጽሐፉ ይበልጥ የተሟላ እንደሚሆን እምነት አለኝ፡፡

በዚህ*ታሪክን በቅኔ* መጽሐፍ ሦስት አካላት እርስበርስ እውቅና ሲሰጣጡ አስተውያለሁ፡፡ እነዚህ አካላትም ደራሲዋ፣ ቀኝ አዝማች ምስጋናው እና ራስ ወሌ ናቸው፡፡ ራስ ወሌ የቀኝ አዝማች ምስጋናውን የግጥምና የቅኔ ችሎታ አይተው የቀኝ አዝማችነትና የሊቀ መኳስነት ማዕረግ ሰጧቸው፡፡ ይህም ራስ ወሌ ሕዝብ ፊት ለቀኝ አዝማች ምስጋናው የሰጡት ዕውቅና ነው፡፡ በዚህም ቀኝ አዝማች ምስጋናውን ከፍ አደረጓቸው፡፡

ቀኝ አዝማች ምስጋናው በተራቸው የራስ ወሌን ታሪክና ሰብዕና በግጥም በመግለጽ አወሷቸው፡ ፡ ይህም ቀኝ አዝማች ምስጋናው በታሪክ ፊት ለራስ ወሌ የሰጡት ዕውቅና ነው፡፡ በዚህም ራስ ወሌን በታሪክ መድረክ ሕያው አደረጓቸው፡፡ ደራሲ በሁሉም አለበል የአያቷን ታሪክና ስራዎች በመሰብሰብ ይህንን መጽሐፍ ለአንባቢ አደረሰች፡፡ ይህም በሁሉም አለበል ቀኝ አዝማች ምስጋናው በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ የክብር ቦታ እንዲያገኙ የሰጠችው ዕውቅና ነው፡ ፡ በዚህም ቀኝ አዝማች ምስጋናውን እንድናውቃቸው፣ እንድናደንቃቸውና እንድናከብራቸው ሆኗል፡፡ በመጨረሻም ለደራሲ በሁሉም አለበል ለዚህ ስኬታማ ስራዋ ያለኝን አድናቆት እገልጻለሁ፡፡

## ዋቢ መጽሐፍ

በሁሉም አለበል (2008 ዓ.ም)፡፡ *ታሪክን በቅኔ፤ ቀኝ አዝማች ምስጋናው አዱኛ (1883-1964)*፡፡ አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች ድርጅት፡፡